# የፕሬዝደንት ኦባማ "ታሪካዊ ጉብኝት"

**አምባገነን አወዳሽ ወይንስ ዲሞክራሲ አጎልማሽ?**

**አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)**

**"ፕሬዝደንት ኦባማ ኢትዮጵያን ለምን ጎበኙ?**

ፕሬዝደንት ኦባማ በስልጣን ላይ ካሉ የአሜሪካ መሪዎች የመጀመሪያው ሆነው ወደ ኢትዮጵያ የሄዱበት ምክንያት "ዱብ እዳ" አይመስለኝም። የኢትዮጲያና የአሜሪካ ግንኙነት የተመሰረተው በብልሁና ዘመናዊው መሪ በአፄ ምኒልክና በአሜሪካው ፕሬዝደንት ቲዎዶር ሮዝቤልት አማካይነት ነው። ኢትዮጵያ በአድዋ የተጎናጸፈችው ድል በዓለም እውቅና እንደሰጣት ታሪክ መዝግቦታል። ይህ ሃቅ ማንም ግለሰብ ወይንም ቡድን ወይንም መንግሥት ሊለውጠው የሚያስችል የሚራል ብቃት የለውም። አሜሪካኖችና ሌሎች መንግሥታት "ምን አይነት የጥቁር መሪ ነው የአውሮፓን ኃያል ለማጥቃት የቻለው" ብለው እንደተነጋገሩ ይታወቃል። በዚያ ወቅት የአረብ ምሁራን ኢትዮጵያ "ልክ እንደ ጀርመኒ በፍጥነት ለማደግ ትችላለች" እንዳሉ አውቃለሁ። ሆኖም አገራችን በውስጥና በውጭ ጠላቶቿ ምክንያት ሰላም አላገኘችም ነበር። ቁም ነገሩ፤ **<u>ከዛሬ ሁለት መቶ አስራ ሁለት ዓመት</u>** በላይ የተመሰረተው የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነት በፋሽስቱ ወረራና በደርግ ፀረ-አሜሪካንነት ፕሮፓጋንዳ ቢበከልም፤ ተከታታይነት አለው። ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት የራሳቸውን አገር ጥቅም ለማስከበር ሙከራ እንዳደረጉ ሁሉ፤ የአሜሪካም መንግሥት የራሱን ጥቅም ለማስከበር ሞክሯል፤ አሁንም ይኼን መርህ ተከትሏል። ፕሬዝደንት ኦባማ የታሪክ፤ የውጭ ግንኙነትና የፖለቲካ ምሁር እንደመሆናቸው መጠን በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የቆየውን ግንኙነት በጽሞና ያውቃሉ። አንድ መንግሥት በሌላ ቢለወጥ ግንኙነቱ የሚቀጥል መሆኑን ይገነዘባሉ ብል ከሃቁ የራቅሁ አይመስለኝም።

ለመሆኑ በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መርሆዎች የቶቹ ናቸው? የትኛው ይቀድማልና ለምን? ሽብርተኞች በአሜሪካ ላይ ያልተጠበቀ ጥቃት ሲያደርሱ፤ የቡሽ መንግሥት በዓለም ዙሪያ ወዳጆች ፈልጎ በአሜሪካ ጥቅም የተመሰረተና ስትራተጂክ የሆነ የቅርብ ወዳጆች ፈጥሯል። ኢትዮጵያ ለዚህ አመችና አስተማማኝ የሆነ አገዛዝ አላት ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ በህወሓት ከሚመራው የኢህአዴግ መንግሥት ጋር ሽብርተኞችን ለማዳከም፤ ቢቻል ለማጥቃት "ቃል ኪዳን" ተገባ። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መርሆዎች **<u>ከሆኑት፤</u>**

**አንድ፤ ሽብርተኞችንና አመፀኞችን መታገልና ማጥቃት፤**

**ሁለት፤ ንግድንና ኢንቬስትሜንትን ማስፋፋት፤**

**ሶስት፤ ከቻይና ጋር አቻ ለአቻ በሆነ ደረጃ መወዳደር፤**

**አራት፤ ድህነትን ለመቅረፍና እርጋታን ለማጠናከር እርዳታ መስጠት፤**

**አምስት፤ በረዢም ጊዜ ስሌትም ቢሆን፤ ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩና ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ስር እንዲሰድ ድምጽ ማሰማትና የተቻለውን ድጋፍ ማድረግ፤**

**ስድስት፤ የአሜሪካን ድጋፍ ለማግኘት የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና የተባበሩት መንግሥታት በአፍሪካ ለሚያደርጉት የጸጥታ እንቅስቃሴ ድጋፍ የሚሰጥ ወዳጅ መንግሥትን መርዳት ናቸው።**

**ከእነዚህ መካከል** አሜሪካ ቅድሚያ የምትሰጠው ለመጀመሪያው ነው። ከዚያ ለንግድ፤ ኢንቬስትመንትና ከቻይና ጋር ለሚካሄደው ውድድር፤ ቀጥሎ ለእርዳታ፤ በመጨረሻ ለሰብአዊ መብቶች መከበር። የእርዳታን መርህ ጠለቅ ብለን ብንመረምር፤ ማንም አገር የሚሰጠው እርዳታ ከራስ ጥቅም ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ይለወጣል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ሽብርተኛነትን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ከተፈለገ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ገዢ ቡድን የገንዘብ፤ የስለላ፤ የጦር መሳሪያ፤ የዲፕሎማሲ ወዘተ ድጋፍ መስጠት አለባት። ራሷ ብቻ ሳትሆን የምትቆጣጠራቸውም፤ እንደ ዓለም ባንክ ያሉ ድርጅቶች እርዳታ የሚሰጡበት ዋና ምክንያት ይኼው ነው። ለኩባ፤ ለሰሜን ኮሪያ፤ ለኢራን እርዳታ አይሰጡም። እኔ የምከራከረው፤ አሜሪካ፤ ሽብርተኛነትን ለማጥቃት ብቻ ( ለአጭር ጊዜ ጥቅም) አፋኝና ጨቋኝ ለሆነው ለህወሓት/ኢህአዴግ "አገልጋይ መሰል" አገዛዝ ድጋፍ እየሰጠች የረዢም ጊዜ ችግርና አደጋ በመፍጠር ላይ ናት በሚል ነው። አፋኝና አሸባሪ አገዛዝ ሽብርተኛነትን ያጠናክራል እንጅ እርጋታን፤ ጸጥታን፤ ሰላምን፤ አብሮ መኖርን፤ አብሮ ማደግን አይፈጥርም። በሳይናይ፤ በግብፅ፤ በሶሪያ፤ በሊቢያ በእየቀኑ የሚሆነውን ማጤን ለዚህ ይረዳል።

የአሜሪካንና የኢትዮጵያን መንግሥታት የሚያዋጣቸው የፀረ-ሽብርተኛውን ዘመቻ ከሰብአዊ መብቶች መከበር ጋር፤ ከመልካም አገዛዝ፤ ከእኩልነትና ከፍትህ፤ ከስልጣን መጋራት አስፈላጊነት ጋር አጣምረው ቢያዩት ነው። ሕዝቡ መብቱ በሚጠይቀው መሰረት ተከብሮ፤ በልቶ ካደረ፤ የተሻለ ኑሮ ከኖረ ሽብረተኞች መግቢያ አይኖራቸውም። የኢትዮጵያ ገዢዎች ሊያደርጉት የሚገደዱት የመጀመሪያው እርምጃ የታሰሩትን ጋዜጠኞች፤ ብሎገሮች፤ የሰብአዊ መብት ታጋዮች፤ የእስልምና ኃይማኖትና የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችንና አባላትን መፍታት ነው የሚለውን እየደጋገምኩ አስመርበታለን። የመሳሪያ ኃይል አንድን አገር ከአደጋ አያድነውም። በአፍሪካ በመሳሪያ ኃይል አቻ የሌለው ደርግ ጸረ-ሕዝብ ስለሆነ ወድቋል። በተጨማሪ፤ የአገሪቱን ግዙፍ ችግሮች ለመፍታት ከተፈለገ፤ ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆነ መገናኛ ብዙሃን ሕጋዊ እውቅና እንዲኖረው ማድረግ፤ ከሃገር የተሰደዱ ጋዜጠኞችና ሌሎች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማድረግና ለደህንነታቸው ዋስትና መስጠት፤ የፖለቲካ ምህዳሩን በማያሻማ ደረጃ መክፈትና የስልጣን መጋራት ስኬታማ እንዲሆኑ መዘጋጀት የሚሉ ሃሳቦች ይገኙበታል።

ፕሬዝደንት ኦባማ እነዚህን ችግሮች አያውቁም ለማለት አንችልም፤ ያውቃሉ። የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤታቸው፤ የስለላና የደህንነት ተቋሞቻቸው ስለ ኢትዮጵያ የማያውቁት አበይት ጉዳይ የለም። የጋበዛቸውንና ተባባሪ የሆነውን ፓርቲ ላለማስቀየም ይሁን ሌላ “የኢትዮጵያ መንግሥት ዲሞክራሳዊ የሆነ የምርጫ ውጤት ነው” ያሉት አግባብ የሌለው፤ ከእውነቱ የራቀና ራስን አገልጋይ ነው። ከጉብኝታቸው ከተመለሱ በኋላ በኦሮምያ፤’ በጋምቤላ፤ በሰሜን ጎንደርና ሌሎች አካባቢዎች የተካሄዱትና አሁን ጸጥ ያሉ ቢመስሉም ነገ ገንፍለው የሚከሰቱ የሕዝብ አመጾች መፍትሄ አላገኙም። ካለፉት የድርቅ ረሃብና የጎርፍ ችግሮች ምንም ያልተማረው ገዢው ፓርቲ የአገሪቱን የፖሊሲና መዋቅራዊ ችግሮች ለመቅረፍ አልቻለም፤ ብቻውን ከቀጠለ አይልችም። የገዢውን ፓርቲ የፖለቲካ ጨዋታ፤ በተለይ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ተካሂዷል የሚለውን ቀልድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፤ የዓለም ሕዝብ አልተቀበለውም።

## የፖለቲካ ቁማር ጨዋታ

ምርጫ ተካሂዶ መቶ በመቶ አሸንፌአለሁ የሚለው ፓርቲ ትዝብትን እንጅ እምነትን አላገኘም። አወዳሾቹም የአሜሪካ ባለሥልጣት ሃቁን አልተናገሩም። የራሳቸው የደህንነት ባለሥልጣን የሆነችው አሜሪካዊት ሱዛን ራይስ የህወሓት መሪ የነበረው ጠቅላይ ሚንስትር ወዳጅ ስለ ምርጫው ሂደትና ገዢው ፓርቲ “መቶ በመቶ አሸንፊያለሁ” ያለውን ተጠይቃ፤ እያሾፈች ከትከት ብላ ስቃለች። ቲያትር ስለሆነባት፤ መልስ አያስፈልገውም ማለቷ ነው። “ዲሞክራሳዊ በሆነ የምርጫ ሂደት የተመረጠ መንግሥት” ያሉትን ብዙ የአሜሪካ ተመልካቾችና ታዛቢዎች ተችተውታል። ምክንያቱም፤ ምርጫው አንዱንም ዓለም የተቀበለው መስፈርት አያሟላም። ሳሙኤል ሃንቲንግተን የተባለው የታወቀ ምሁርና ደራሲ፤ “**Dead Souls: the denationalization of the American elite,** the National Interest, 2002 በተባለው ጽሁፉ እንዲህ ብሏል። “Elections, open, free and fair, are the essence of democracy, the inescapable sine qua no (የዲሞክራሲ መሰረት አንድ ብቻ ነው። ያልተዛባ፤ ክፍት፤ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ይባላል፤” ከዚህ ውጭ ምርጫ ለይስሙላ ብቻ ነው። የፎርብስ ጋዜጠኛው ማይክ ጎንዛሌዝ ፕሬዝደንቱ የተናገሩት አስገርሞትና አስቆጥቶት እንዲህ ብሏላ። “For Obama to make excuses for Hailemariam Dessalegn government’s horrendous human rights record by calling the country’s past hardships and the relative infancy of its Constitution” is inexcusable. የህወሓት/ኢህአዴግን “ጨካኝና ኢ-ሰብአዊ” የሆነ የመብቶች ረገጣና አፈና ካለፈው መንግሥትና ሁኔታ ጋር ማመዛዘን አግባብ የለውም። ለዚህ ለሚዘገንን አገዛዝ” ድጋፍ እንደ መስጠት ነው ብሏል። የአሁኑ አገዛዝ መነጻጸር ያለበት ከቦትስዋና፤ ከሞሪሸስ፤ ከጋናና ከሌሎች በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉ ዲሞክራሳዊ ሃገሮች ጋር ነው። በተጨማሪ፤ ራሳቸው ከተናገሩት ትችት ጋር ሲነጻጸር ምንም ግንኙነት የለውም።

አንዳንድ ታዛብዎች፤ ምርጫው ሲካሄድ፤ “እንደ ሌሎች ሃገሮች ብጥብጥ አልነበረም፤ ሰው አልሞተም፤ መራጮቹ ጨዋነት አሳይተዋል” ወዘተ የሚለውን መሰረት አድርገው ይሆናል ይላሉ። ይኼ አያስኬድም። የማያስኬድበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ስለታፈነና ሕዝቡ መከራም ተሸክሞ ጨዋነቱን ስለማይረሳ ጭምር ነው። የረጋ አእምሮና ባህል ያለው፤ በጎሰኝነት ያልተበከለና መንፈሳዊ ሕዝብ ነው። ብጥብጥ አለመኖሩና ሰው አለመሞቱ ምርጫውን ዲሞክራሳዊ አያደርገውም።

ወደ አወንታዊው አቀራረባቸው ከመዞሬ በፊት፤ እንደ ተመልካች ሆኘ ያየሁት የንግዳ ያቀባበል ትዝብት አለ። ኢትዮጵያዊያን ከሚታወቁባቸው እሴቶች መካከል የእንግዳ አቀባበል አንዱ ነው። ዓለም ባንክ ስሰራ ማርቲን ሬቫሊየን የተባለ የጥናትና ምርምር ዲሬክተር የነገረኝ ትዝ ይለኛል።

## ጨዋ ሕዝብ ግፈኛ አገዛዝ

የድህነትን አስከፊነት ለማጥናት ገጠር ይሄዳል። አንዲት ምስኪን እናትን ያነጋግራል። “አይ፤ ከመነጋገራችን በፊት ምሳ መብላት አለበወት ብላ፤ ያላትን አንዲት ዶሮ አርዳለሁ” ትላለች። ፈረንጁ “እንዴት ይሆናል፤ የተገላቢጦሽ” ብሎ ያስቸግራል። “አይ፤ እኔ ደሃ ብሆንም ክብር አለኝ፤ እርሰወ እንግዳየ ነወት፤ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ፤ ባህሌን አከብራለሁ” ብላ ዶሮዋን አርዳ ምሳ ጋበዘችው። እጅግ በጣም ተደንቆ ጎጆዋን አክብሮና አመስግኖ የዶሮዎች መግዣ የሚሆን ገንዘብ ለአስተርጓሚው ሌላ ጊዜ እንዲሰጥለት ትቶ ተሰናበተ። ድሃውም ሆነ ኃብታሙ እንግዳን የማክበርና የማስተናገድ ልምዱና ባህሉ አሁንም እንዳለ ነው።

በመንግሥት መሪ ጉብኝት፤ የኢትዮጲያ መንግሥታት ያለ የሌላቸውን ወጭ እንደሚያፈሱ አስታውሳለሁ። የአገር ክብር ከዋጋ በላይ ስለሆነ። አፄ ኃይለ ሥላሴ የአፍሪካ አንድነት ማህበርን ሲያስመሰርቱ መሪዎችን በሚያስደንቅ አቀባበል እንዳስተናገዱ አስታውሳለሁ። ቲቶ፤ ናስርና ሌሎች እንግዶች ሲጎበኙ አቀባበሉ ሃገሪቱ ካላት አቅም በላይ መሆኑን አስታውሳለሁ። የኢትዮጵያ ክብር ከፍተኛ መሆኑን የተገነዘቡት አጼ ኃይለ ሥላሴ የአፍሪካን አንድነት ህንጻ በአገሪቱ ወጭ የሰሩበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያን የነጻነት ታሪክና ክብር ለማረጋገጥና ለማጠናከር ነበር።

የመጀመሪያው የአሜሬካ መሪ በኦፊሴል ደረጃ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ከፍተኛ ዝግጅት ይደረጋል፤ እንግዳው ሕዝብ እሳቸውን በሚያይበት ሰዓት ይመጣሉ፤ ለሕዝብ ንግግር ያደርጋሉ ወዘተ የሚል ግምት ነበረኝ። ሕዝብ አበባ ይዞ እንደማይቀበላቸው አውቃለሁ። እንዲያውም ሰልፉን ተጠቅሞ “ሌባ፤ ሌባ፤ አፋኝ፤ አፋኝ፤ ጎሰኛ” ወዘተ እንደሚል እገምታለሁ። አቀባበሉ ለታላቋ የአሜሪካ መሪ አግባብ አለው ወይንስ የለውም የሚለውን ጡሮታ ሲወጡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲገልፁ ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ። ከሄዱ በኋላ ይሁን ከመሄዳቸው በፊት የአሜሪካ ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት የትግርኛ ሙዚቃ እየሰሙ እንዲደንሱ የተደረገው ትይንት የአቀባበሉን ግድፈት አያሻሽለውም፤ ያባብሰዋል። አዲስ አበባ መቀሌ አይደለም። ቪዲወውን ሳይ፤ እራሴን “ምን መልእክት ለመስጠት ነው” ብየ ጠየቅኩ፤ ገዢዎቹ እኛ ህወሓቶች ነን ለማለት ነው? እንኳን ወደ “አዲሲቷ በጎሰኛነት፤ በጠባብ ብሄርተኝነት የተከፋፈለችና የተበለችው ኢትዮጵያ” መጣችሁ ለማለት ነው? ወይንስ፤ እመኑን፤ ከእናንት ጋር መደነሳችን

እንቀጥላለን?" እርዱን ለማለት ነው? ኢትዮጵያን የሚጎበኝ ፈረንጅ ወይንም ሌላ ስጦታ ሳይሰጠው፤ ሳይሰጣት የተመለሰ፤ የተመለሰች ፈልጎ ለማግኘት አይቻልም። ዳንሱና ዋካታው አገሪቱ ከሁለት አቅጣጫዎች የገጠማትን አደጋዎች ሊሸፍን አይችልም።

አንዱ አደጋ የአገር ውስጥ አለመግባባት፤ መከፋፈልና የእርስ በርስ ግጭት ነው፤

ሁለተኛው አደጋ የውጭ ኃይሎች፤ መንግሥታትን ጨምሮ የሚታየው ከበባና የሚያደርጉት ከፍተኛ ጫና ነው። እነዚህ ድርብ አደጋዎች ሊያመጡ የሚችሉትን መጥፎ ውጤት አሜሪካኖች ልብ አላሉትም ለማለት ባይቻልም የኢትዮጵያ መንግሥት አገልጋይ እስከሆነ ድረስ ትኩረት አልሰጡትም፤ ወደፊትም አይሰጡትም። የማቀርበው ሃሳብ መከፋፈል ለአገር ነጻነትና ሉዐላዊነት ጸር መሆኑ በግልጽ የሚታይ መሆኑን ነው። ለዚህ መፍትሄው በአንድነት ለመስራት ውሳኔ ማድረግ ብቻ ነው።

**በማንዴላ አድራሽ ያደረጉት ንግግር ምን መልእክት አቀረበ?**

**ስለሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት**

"የተናገርኩት ሁሉ-- ሁሉን አቀፍና ዘላቂንነት ያለው እድገት፤ ልማት፤ ደህንነት-- ስኬታማ ሊሆን የሚችለው መልካም አገዛዝ ሲኖር ብቻ ነው። ይኼን ከኢትዮጵያ ባለ ሥልጣናት ጋር በግልጽ ተነጋግረናል። በተያያዘና የጦፈ ውድድር ባለበት የዓለም ኢኮኖሚ ዘመናዊ መገናኛ፤ የማህበረሰብ ቴክኖሎጅና ነጻ የዜና/የእውቀት ስርጭት ወሳኝ ነው። እኔ የማምነው የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ድምጽ ሲሰማና ሲከበር፤ ሁሉም ዜጎች በሃገራቸው የፖለቲካ ጉዳይ ለመሳተፍ ሲችሉ አገር ጠንካራና የበለፀገች ትሆናለች የሚል ነው። ይኼን በሚመለከት የኢትዮጵያ መንግሥት ሊወስዳቸው በሚገባው ፖሊሲዎች ላይ፤ ለምሳሌ፤ የመልካም አስተዳደር፤ የመሰረታዊ ነጻነትና የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት፤ የዲሞክራሲ ሂደት መጠናከር ጥልቀት እንዲኖረው አሳስቤአለሁ።" ይኼን በቃለ መጠይቅ የተናገሩትን አስኳል ጉዳይ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ባቀረቡት ንግግር አጠናክረውታል። ሆኖም ከወራቶች በኋላ አንድም ለውጥ አይታይም። ጫና አላደረጉም ማለት ነው።

በተጨማሪ "ለጠቅላይ ሚንትስር ኃይለማሪያም ደሳለኝ እንዳልኩት፤ ባለፈው ምርጫ ብጥብጥ አለመኖሩ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ናት ለማለት አያስችልም፤ ጉዞው መጀመሩን ያሳያል። በእኔ እምነት፤ ኢትዮጵያ ጋዜጠኞችን ካሰረችና እንዳይንቀሳቀሱ ከከለከለች፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለ ምንም እገባና አፈና እንደልባቸው በፖለቲካው ለመሳተፍ ካልቻሉ፤ እምቅ የሆነው የማደግ ኃይሏን ለራሷ እድገትና ልማት ለመጠቀም አትችልም... ዲሞክራሲ ለይስሙላ ምርጫ ማካሄድ መሆን የለበትም... ጋዜጠኞች ስራቸውን ሲሰሩ ማሰር፤ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ተቆርቋሪዎችን በወንጀለኛነት እንዲከሰሱ ማድረግና ማሳደድ፤ የማህበረሰብ ድርጅቶችን ማፍረስ ወዘተ የኢምንት ያህል ዲሞራሳዊ ስርዓት መኖሩን አያሳይም።" ከዚህ ጋር ጨምረው ያስተላለፉት መልእክት የአምባገነኖች መሪነት ጎጅ መሆኑንና ግለሰብ መሪዎችና ፓርቲዎች በተከታታይ ራሳቸውን መተካት መቆም እንዳለበት ነው። "አፍሪካ ጠንካራ ተቋሞች እንጅ ግለሰቦች አያስፈልጓትም። ግልጽ ላድርገው። መሪዎች (ፓርቲዎች) ስልጣን አንልቅም ሲሉ የሚፈጥሩት ችግር ቀላል አይደለም። አንለቅም የሚለው ፈጽሞ አይገባኝም። እኔ፤ ፍላጎትም ቢኖረኝ፤ በአሜሪካ ሕገ መንግሥት እገዛለሁ፤ ሶስተኛ ጊዜ ለመወዳደር አልችልም።"

ስልጣን የጊዜ ገደብ ያስፈልገዋል ማለታቸው ነው። ሆኖም ከጎበኙበት ወዲህ ያለውን ሁኔታ ያባባሰወው ሁለቱን የአገር ውስጥና የውጭ አደጋዎችን ነው። ህወሓቶች በተከታታይ አምስት ምርጫዎችን "አሸንፊያለሁ" የሚለውን ሃሰት በቀጥታ ይመለከታል። ምርጫዎቹ ነጻና ፍትሃዊ ቢሆኑ ኖሮ የጋምቤላ፤ የኦሮምያና የሰሜን ጎንደር ሕዝብ "አሻፈረኝ፤ ግፉ በዛብኝ፤ አፈናው ይቁም" አይልም ነበር። የኢትዮጵያ ድንበር አይደፈርም ነበር። በጋምቤላና ሌሎች ቦታዎች የእርስ በርስ እልቂት አይካሄድም ነበር።የሱዳን መንግሥት ወገኖቻችን ደፍሮ አፍኖኖና አስሮ አይማርክም ነበር። አረቦች በአሰብ የጦር ምሽግ ለመስራት አይደፋሩም ነበር። ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ተቆርቋሪ መንግሥት እንደሌላት ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ፤ የአባማ መንግሥት በቅርቡ ያጠናከረው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰብአዊ መብት መከበር አይደለም። በአሜሪካና በኢትዮጵያ ያለውን የጸጥታ፤ የደህንነትና የጸረ-ሽብርተኛ ዘመቻውን ውል ነው። የተሰጠው ምልክት አፈናው ተቀባይነት እንዳለው የሚደግፍ ይመስላል።

**ስለ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ አስፈላጊነት**

ፐሬዝደንት ኦባማ ለአፍሪካ መሪዎች የማያሻማ መልእክት አቅርበዋል። "በእኔ እምነት የአፍሪካ እድገት አስተማማኝ የሚሆነው ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ሲመሰረት ብቻ ነው። እንደ ሌላው የዓለም ሕዝብ አፍሪካዊያን የራሳቸውን ህይወት ለመቆጣጠርና ለመምራት መቻል አለባቸው። የእያንዳዱ ዜጋ ክብር በሕግ እውቅና ማግኘት አለበት። ዲሞክራሲ መስፈርቶች አሉት---ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ፤ የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ የመንቀሳቀስ፤ የመደራጀት፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ--መብቶች መከበር አለባቸው። እነዚህ መብቶች በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት እውቅና አግኝተዋል። ለምሳሌ፤ የአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች ቻርተር "እያንዳንዱ ግለሰብ ሰብእነቱና ሰብአዊ መብቱ መከበር አለበት። ሴራ ሊኦን፤ ናምቢያ፤ ቤኒን፤ ቦትስዋና፤ ጋና፤ ደቡብ አፍሪካ የዲሞክራሲ መሰረት ጥለዋል። በናይጀሪያ፤ ሃያ ስምንት ሚሊየን ሕዝብ ድምጽን ሰጥቷል...ባጭሩ፤ የአፍሪካ መንግሥታት የሕዝባቸውን መብት ካላስከበሩና ካላከበሩ ከቅኝ ገዢዎች ነጻ ሆነናል ለማለት አይችሉም።" ይህን ማለት ቀላል ነው። የአሜሪካ መንግሥት የሚሰጠው ግዙፍ እርዳታ ዲሞክራሳዊ ስርዓትን ለመመስረት ያስችላል ወይንስ አምባገነን መንግሥታትን ያጠናክራል?

እስካሁን ያየነው የአሜሪካ መንግሥት በሚናገረውና በሚሰራው መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ ነው። ለዚህ ጥንካሬ የሰጠው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሌሎች አብሮና ተባብሮ ለመስራት አለመቻል ነው። ችግሩን ካወቅን ለምን ተባብረን ለመስራት እንደማንችል አይገባኝም። የድብቅ አጀንዳ አለን ወይንስ የለንም? እንባቢ ያስብበት።

ፕሬዝደንቱ ዲሞክራሳዊ መንግስታት ሁሉን ችግር ይፈታሉ አላሉም። "ማንም ሃገር፤ አሜሪካን ጭምሮ፤ ሁሉን ነገር አስተካክሏል ለማለት አይቻልም...የማይካደው፤ የዜጎች መብት ከተጣሰ ሁላችንም የመናገር ሃላፊነት አለብን... አንዳንዴ፤ የእኛ ወዳጆች በሆኑ መንግሥታት ላይ የምናደረገው ትችት ለዚህ ነው።" ችግሩ ከንግግሩ ላይ አይደለም፤ ከድርጊቱ ላይ ነው። ሰብአዊ መብቶች በተደጋጋሚ ሲታፈኑና ለውጥ የሚፈልጉ ሁሉ በጸረ-ሽብርተኛነት ሲታሰሩ የመሳሪያ፤ የስለላ፤ የመረጃ፤ የመከላከያና ሌላ ድጋፍ መስጠቱ የሚጎዳው ኢትዮጵያንና መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ነው። ዘላቂነት የሚኖረው መርህ ለሰብአዊ መብቶች የሚሰጥ ድጋፍ ነው።

**የተዛባ ገቢና ኃብት፤ የተዛባ እድገት አስጊነት**

"ዛሬ አፍሪካን የገጠማት ፈተና ለአሁኑና ለወደፊቱ ትውልድ የስራ እድል ለመፍጠር አለመቻሏ ነው...ይኼ ጊዜ የማይሰጥ የማህበረሰብ ችግር ሆኗል...እያንዳንዱ ሃገር ብዙ ሚሊየን የስራ እድል መፍጠር አለበት....ኢኮኖሚስቶች እንደሚነግሩን፤ ወጣት ትውልድ ያለበት ሃገር በፍጥነት ያድጋል..ለማደግ ትምህርትና ጉልመሳ ያስፈልጋል፤ የስራ እድል መፈጠር አለበት" ብለው እድገት ለጥቂቶች ገቢ፤ ኃብትና ኑሮ መሻሻል ብቻ ከዋለ አደጋ እንዳለው አስምረውበታል። "እድገት ማህበራዊ ጥቅምና ዘላቂነት የሚኖረው ውጤቱ በጥቂቶች፤ ለጥቂቶች ሲሆን አይደለም። የመስራትና የራስን ስራ የመፍጠር እድል መስፋፋት አለበት....ወጣቱ ትውልድ እድልና ድጋፍ ካገኘ፤ አስደናቂ ውጤት ያስገኛል።" ካላገኘ ይሰደዳል፤ ለሃገርና ለቤተሰብ ሸክም ይሆናል። ንግግራቸውን ካቀረቡ ወዲህ የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ስደት በባሰ ሁኔታ ቀጥሏል። በኦሮምያ የተካሄደው ግፍ ብዙ ሽህዎች ወገኖቻችን እንዲሰደዱ አድርጓል። ተሰደንም ለመተባበር አለመቻላችን ለጥቃት ከፍተኛ ግብዓቶ ከሆነ ቆይቷል።

**የሙስናና ከሕግ ውጭ የሚሸሽ ኃብት አድካሚነት**

በአህጉር ደረጃ ሲነጻጸር እንደ አፍሪካ ለስርቆት፤ ለጉቦ፤ ለሙስናና ከሕግ ውጭ ከድሃው ሕዝብ እየተዘረፈ ወደ ውጭ ለሚሸሽ ግዙፍ ኃብት የተመቸ የዓለም ክፍል የለም። ጥናት ያደረጉ ተቋሞችና ምሁራን አፍሪካ በየዓመቱ **<u>ከ$300 እስከ $400 ቢሊየን</u>** እንደምትዘረፍ መረጃዎች አቅርበዋል። ሁኔታው ያሳሰባቸው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽን ያቀረቡት ዘገባ አፍሪካ እየደማች መሆኑን ያሳያል። የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝደንት ኢምቤኪ የመሩት ጥናት ግዙፍ ሃብት ከሚሸሽባቸው አገሮች **<u>መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆኑና ገልፀዋል። ባለፉት አራት ዓመታት ብቻ $10</u>** ተዘርፋለች። ይኼ ኃብት ስንት ፋብሪካዎች፤ ስንት የመስኖ ግድቦችና ሌላ እንደሚሰራና ለስንት ሚሊየን ኢትዮጵያዊያን የስራ እድል እንደሚፈጥር ለመገመት አያዳግትም። በአሁኑ **<u>ወቅት ከ18-20 ሚሊየን</u>** ሕዝብ በድርቅና ሌላ ረሃብ የውጭ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው የኢህአዴግ መንግሥትም ይቀበላል። በተጨማሪ ከ100,000-500,000 ሕዝብ በጎርፍ ምክንያት እርዳታ ያስፈልገዋል። አስደናቂው የአገሪቱ እድገት ውጤት ይኼን ግዙ የሆነ የተፈጥሮ ችግር በኢትዮጵያ አቅም ለመወጣት አልቻለም። የማይችልበት አንዱ ምክንያት ግዙፍ ኃብት ከአገር ተሰርቆ ስለወጣ ነው። በተጨማሪ፤ ምንም ለፈፋ ቢደረግ ገዢው ፓርቲ ችግሮቹን አስቀድሞ ለመቋቋም መሰረታዊ እርምጃዎችን አልወሰደም። ለምሳሌ፤ ዝናብ ሲዘንብ ቋቶችን መገንባት። ለከፉ ጊዜ የሚሆኑ ጎተራዎችን አለመሙላት። የገጠሩ ሕዝብ ሌሎች የስራ እድሎች እንዲኖሩት፤ ለምሳሌ ኢንዱስትሪ፤ አለመስፋፋቱ ይገኙበታል።

የተፈጥሮ ችግሮች፤ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስን አገሪቱን እያደሙ መሆናቸው አያከራክርም። የኢትዮጵያ እድገት ከድርብ አሃዝ ወደ 4.5 በመቶ የሚወርድበት አንዱ ምክንያት የወደመውን መተካት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

ፕሬዝደንት ኦባማ "አፍሪካ ያላትን እምቅ የእድገት ጥሪት ለመጠቀም ከፈለገች የሙስናን ካንሰር ማቆም አለባት" ብለዋል። እስማማለሁ፤ መጻህፍት ጽፌበታለሁ። ችግሩ፤ የውጭ ንግድ፤ ኢንቬስትመንት፤ እርዳታ፤ ከስደተኛው የሚላክ የውጭ ምንዛሬ ለሙስናና ከሕግ ውጭ ለሚሸሽ ኃብት ግብአት መሆኑ ጭምር ነው። ከሕግ ውጭ የሚሸሸው ኃብት መደበቂያ ያስፈልገዋል። የምእራብ፤ የመካከለኛው ምስራቅ፤ የኤዝያና የላቲን አሜሪካ/ካሪብያን ባንኮች መደበቂያ ናቸው። ስለሆነም፤ የአሜሪካና ሌሎች መንግሥታት የሚሰረቀውና የሚሸሸው ገንዘብ ወንጀል መሆኑንና መግቢያ እንዳያገኝ ለማድረግ የበለጠ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ሙስናና ከሕግ ውጭ የሚሸሸው ኃብት ስርዓት ወለድ ነው። ባለ ስልጣናት ተጠቃሚዎች ናቸው። የአፍሪካ መንግሥታት መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው ራሳቸው ሙሰኛ ከሆኑ ሙስና ሊገታ አይችልም። ስለዚህ፤ አገዛዙ መለወጥ ይኖርበታል። አሜሪካኖች ስርዓቱ እንዲለወጥ ጥረት ያደርጋሉ ማለት ዘበት ነው፤ አገልጋይና ታዛዥ የሆነ መንግሥት እስካለ ድረስ አድርገው አያውቁም። ፍትህ የሚፈልግ ሕዝብ ራሱ መታገል አለበት፤ ይህ ሲሆን የውጭ ድጋፍ የማይቀር ነው።

**ከህወሓት/ኢህአዴግ የተለየ የፖሊሲ መርህ ጉዳይ**

ፕሬዝደንት ኦባማ ከህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ጋር መለስተኛ ልዩነት እንዳላቸው አልደበቁም። "እኛ ከልዩ ልዩ ታላላቅ ሃገሮች ጋር ግንኙነት አለን...ለምሳሌ፤ ቻይና፤ በምንጋራቸው ጉዳዮች ላይ አብረን የመስራት መብት አለን፤ ልዩነቶቻችንም እንገልጻለን... ሽብርተኛነትን በሚመለከት፤ አንዳንድ በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ የመንግሥት ተቃዋሚ የሆኑ ወይንም ለውጥ እንዲመጣ" የሚታገሉ ክፍሎች እንዳሉ" እናውቃለን። እነዚህ ለኢትዮጵያ መንግሥት አስጊ መሆናቸው ይገባናል። ሆኖም የእኛ የመረጃና የስለላ ድርጅቶች እነዚህ እንቅስቃሴዎች "ሽብርተኛ" ወደሚያስብል ደረጃ መድረሳቸውን አይቀበሉም። ስለ አበይት ጉዳዮች መናገራቸው፤ መንግሥትን መቃወማቸውና እንደ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መንቀሳቀሳቸው መብታቸው ነው። እኛ እነዚህን ለዲሞክራሲ የቆሙ እንቅስቃሴዎች እንከበከባለን" የሚል ግልጽ አቋም አቅርበዋል።

አሁንም ወሳኙ ይኼ አባባል ተግባራዊ ሲሆን ነው።

በአጠቃላይ ፕሬዝደንቱ በማያሻማ ደረጃ ለዲሞክራሳዊ ለውጥ ያላቸውን ድጋፍ፤ ተስፋና ምኞት ገልፀዋል። ሆኖም፤ ይኼን ስኬታማ ሊያደርግ የሚችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ነው። **<u>ዛሬ ከተጠቃሚዎች</u>** ውጭ በየትኛውም የኢትዮጵያ "ክልል ወይንም ብሄር" በራሱ መንግሥት ላይ ያላኮረፈ፤ የማይማረር፤ በይፋ የማይበሳጭ፤ ያልተቆጣና ለውጥ ያስፈልጋል የማይል ዜጋ ፍልጎ ለማግኘት አይቻልም። የውጭ ታዛቢዎች ከኢትዮጵያ ሲመለሱ የሚናገሩትም ይኼን ነው።

*ታዲያ ለምን ብሄራዊ የሆነ ውይይትና ድርድር አልተቻለም? አሜሪካኖችና ሌሎች የውጭ መንግሥታት ምን ለማድረግ ይችላሉ?*

በአሜሪካ የምንኖር ለመምረጥና ለመመረጥ መብት ያለን ትውልደ ኢትዮጵያ ልንገፋቸው የምንችለው ሁኔታዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል ዋናው የሚካሄደው የፕሬዝደንትነትና የምክር ቤት አባላት ምርጫ መካሄዱ ነው። ይህን እድል በያለንበት አካባቢ በግልና በጋራ ለመጠቀም መቻል አለብን።

**የአሜሪካ መንግሥት ሊያደርገው የሚችለው እርምጃ**

አንድ፤ የአሜሪካን የዲፕሎማቲክ፤ የእርዳታ፤ የመሳሪያ፤ የስለላና ሌላ አቅማና ድጋፍ መሰረት አድርጎ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብር፤ ጎሳዊ አድልዎንና ሙስናን እንዲያቆም፤ ጋዜጠኞችንና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችን እንዲፈታ ያልተቆጠበ ጫና ማድረግ፤

ሁለት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሽብርተኛነት ወንፊት የሆኑ ድርጊቶችን እንዲያቆም ማድረግ፤ ለምሳሌ፤ ዜጎችን ከቀያቸው ማባረር፤ የዘር ማጥፋትና ማሳደድ፤ ተቃዋሚዎች ድምጽ ስላሰሙ ከማሳደድ እንዲቆጠብ፤

ሶስት፤ በአገር ቤትና ከአገር ውጭ ለሚንቀሳቀሱ የሰብአዊ መብት ታጋዮችና የዲሞክራሲ ጠበቃዎች የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፤ በገንዘብ መርዳት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭ በሚኖሩ በአሜሪካ ዜጎች ላይ የሚያደርገው ክትትል ከሕግ ውጭ መሆኑን በይፋ መናገር፤ ማጋለጥ፤ ክሶች ለመመስረት የሚፈልጉ ክፍሎችን ማበረታታ፤

አራት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለብሄራዊ መግባባት፤ ለእርቅና ሰላም ውይይት፤ ከዚያም ለስልጣን መጋራት ፈቃደኛ እንዲሆን ማመቻቸት፤ ጫና ማድረግ።

**የአሜሪካ ምክር ቤት ሊወስድ የሚችለው እርምጃ**

ከዚህ በፊት በሰብአዊ መብቶች መከበር፤ በሕግ የበላይነት፤ በኢኮኖሚ ነጻነት፤ በደህንነትና በዲሞክራሲ አስፈላጊነት ተጀምሮ የነበረው ሕግ እንዲያንሰራራ ጥረት ማድረግና የአሜሪካ ሴናተሮች የጻፉትን ግልጽ ደብዳቢ መደገፍ፤ ማስተጋባት፤ ሌሎች እንዲደግፉት ጫና ማድረግ፤

ለዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ያልተቆጠበ የባጀት ድጋፍ እንዲሰጥ መጎትጎት እና፤

የአሜሪካ እርዳታ ከሰብአዊ መብቶች መከበር ጋር እንዲያያዝ ማድረግ።

**የኢትዮጵያ መንግሥት ሊያደርገው የሚገባው እርምጃ ጫናዎች**

አንድ፤ ኢትዮጵያዊያን በሰላም እስከተንቀሳቀሱ ድረስ፤ ያለ ምንም ገደብ የመናገር፤ የመንቀሳቀስ፤ የመጻፍና የማሳተም፤ የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፤ የድጋፍ ገንዘብ የመሰብሰብ፤ የፈለጉትን ኃይማኖት የመከተል መብታቸው ሙሉ በሙሉ እንዲከበር የማድረግ ኃላፊነት እንዲያሳይ ጫና ማድረግ፤

ሁለት፤ የፖለቲካ ምህዳሩ መዘጋት ለኢትዮጵያ አደገኛ መሆኑን ተረድቶ የፖለቲካው ምህዳር ሙሉ በሙሉ እንዲከፈት የተባበር ጭና ማድረግ፤

ሶስት፤ ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ በሕግ ፊት እኩል መሆኑን ተቀብሎና አምኖ ፍትሃዊ በሆነ መልክ ማስተዳደር፤ ማንም ግለሰብ ከሕግ በላይ ሆኖ የሚያደርገውን ወንጀል በሕግ ፊት ማጋለጥ፤

አራት፤ ከመንግሥትና ከፓርቲ ቁጥጥር ነጻ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን ባህልና ልምድ መሰረት እንዲይዝና ጋዜጠኞች፤ ብሎገሮች ያለምንም ገደብ እንዲቀሳቀሱ መፍቀድ፤ የተሰደዱ ጋዜጠኞች ፍላጎት ካላቸው እንዲመለሱ እንዲጋብዝ ጭና ማድረግ፤

አምስት፤ የጸረ-ሽብርተኛውና የማህበረሰብ ሕጎች እንዲሻሻሉ፤ የማፈኛ መሳሪያ እንዳይሆኑ ጫና ማድረግ፤ ከመንግሥትና ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ የሆኑ የማህበረሰብና ሌሎች ተቋሞች መሰረት እንዲይዙና ሕዝቡን እንዲያገለግሉ እንዲፈቅድ ማስገደድ፤ ካልተስማማ በያቅጣጫው እገባ እንዲካሄድ ዘመቻ ማድረግ፤

ስድስት፤ የጸረ-ሙስናው ኮሚሽን በሞያቸው በታወቁ ግለሰቦች ከመንግሥትና ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ ሆኖ እንዲሰራ ማስገደድ፤ ማንም ኪራይ ሰብሳቢ፤ ሙሰኛና ከሕግ ውጭ ኃብት ያሸሸ ግለሰብ ወይንም ቡድን በሕግ እንዲጠየቅ ጫና ማድረግ፤ ገንዘብ የሚሸሽባቸው አገሮች የምያሸሹት ግለሰቦች ስም ይፋ እንዲያደርግ ጥረት ማድረግ፤

ሰባት፤ በቂም በቀል፤ በጎሳና በኃይማኖት ጥላቻ፤ በዛቻና በማስፈራራት የሚደረገው የፖለቲካ ባህል ለኢትዮጵያ ህልውናና ለሕዝቧ አብሮ መኖር አደገኛ ስለሆነ ይኼን ጎታችና ኋላ ቀር የፖለቲካ ባህል በአስቸኳ እንዲቆም የተባበረ ጥረት ማድረግ፤

ስምንት፤ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ አቅምና ጥሪት ሙሉ በሙሉ ተጠቅማ ከረሃብ፤ ከድህነትና ከጥገኝነት ነጻ እንድትሆን፤ አገር ተከል የሆነ የግል ክፍል እንዲያብብ ጫና ማድረግ፤

ዘጠኝ፤ ሁሉን አሳታፊ የሆነ የእርቅና የሰላም ድርድር በአስቸኳይ እንዲካሄድ ፈቃደኛ እንዲሆን፤ ተቃዋሚ ክፍሎች የድርድሩ አጋር እንዲሆኑ፤ ብሄራዊ ችግሮችን አብረው እንዲፈቱና ወደ እውነተኛ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ለመሸጋገር እንዲቻል አግባብ ያላቸውን የፖለቲካና ሌሎች ክፍሎች ያካተተ ብሄራዊ የአንድነት መንግሥት ለማቋቋም ፈቃደኛ እንዲሆን ከፍተኛ ዘመቻ ማካሄድ፤

አስር፤ ተቃዋሚውን ሁሉ ከማውገዝ ተቆጥቦ እነዚህ ኃይሎችና ድምፆች የሚያቀርቧቸውን አማራጮች እንዲያስተናግድ ለአበዳሪዎች፤ ኢንቬስተሮችን መንግሥታት አቤቱት ማቅረብ፤

አስራ አንድ፤ በውጭ ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለዲሞክራሲ በሚታገሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ላይ የሚደረገውን ክትትል በአስቸኳይ  እንዲቆም ዘመቻ ማካሄድ።

**የተቃዋሚው ክፍል ሊያደርገው የሚገባው**

አንድ፤ የእርስ በርሱን የፖሮፓጋንዳ ጦርነት በአስቸኳይ ማቆም፤

ሁለት፤ የመተማመን፤ የመከባበርና የመደማመጥ ፖለቲካ ባህል ልምድ እንዲሆን ጫና ማድረግ፤

ሶስት፤ በተናጠል የሚደረገው ትግል የትም እንደማያደርስ ተገንዝቦ አበይት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተባብሮና ተቻችሎ መስራት፤

አራት፤ በዲፐሎማሲ የሚደረገው ጥረት ተደማጭነት የሚኖረው በመተባበርና በአንድነት በመስራት ብቻ ስለሆነ ተወያይቶ ዘላቂነት ያለው ዓለም አቀፍ ተቋም መፍጠር፤

አምስት፤ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚገኙ ተቃዋሚዎች ሁሉ በአንድ ለይ ተሰብስበው የጋራ መርህ እንዲያወጡ አስቸኳይ ግፊት ማድረግና፤

ስድስት፤ ኢትዮጵያን ከመፈራረስና ሕዝቧን ከእርስ በእርስ ግጭት ለማዳን ተባብሮ መነሳት።

Ssemegn@yahoo.com